የDPS ወላጆችና አሳዳጊዎች፣

ዴንቬር የህዝብ ት/ቤቶች ለአስተማሪዎች፣ለሠራተኞች እና ለተማሪዎች አሁን *የጉግል አፕስ ኃይል ለትምህርት* (*Google Apps for Education.*) ማዘጋጀቱን በኩራት እናስታውቃለን። ይህ ለትብብር መሳሪያዎችን ((Google Docs)፣መገናኛ (Gmail)፣እና በእንቴርኔት የሰነድ ማጠረቀሚያ (Google Drive)) በማቅረብ የመማሪያ ክፍሎችን ይደግፋል። በ2013-2014 የትምህርት ዓመት በመጀመር፣ ለተማሪዎ ካልፈለጉ በስተቀር ሁሉም ተማሪዎች የተማሪየጉጉል ሂሳብ ይሰጠዋል።

***<u>ይህ ማለት ምን ማለት ነው</u>***

ይህ ማለት ት/ቤቶች ለክፍል *ሥራና* ለግኑኝነት ጉግል አፕስ የመጠቀም ምርጫ አላቸው። ተማሪዎች በድስትርክቱ ደህና የጉግል ሂሳብ ይሰጣቸዋል። ት/ቤታቸው ይህንን ሂሳብ ለመጠቀም ዝግጁ ሲሆን፣ወላጆች ይነገራቸዋል እና ተማሪዎች ጉግል አፕስ እንዲጠቀሙ ሥልጠና ይሰጣቸዋል።

***<u>ይህ የሚሆነው መቼ ነው?</u>***

የድስትርክቱ ሠራተኞች ይህንን ዘዴ በሥራ ላይ ለማዋል በዚህ በ2013 የበጋ ወቅት እየሠሩ ናቸው። ት/ቤቶች ሂሳቡን በትምህርት ዓመት መጀመሪያ ላይ መጠቀም ይጀምራሉ እና አገልግሎቱን ሲጀምሩ ለወላጆች ይነገራቸዋል።

***<u>ወላጆች ምን ማድረግ አለባቸው?</u>***

ከተማሪዎ ት/ቤት ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ይጠባበቁ። እግረ መንገዳችሁንም፣ጉግል አፕስ ለትምህርት ስላለው ዋጋ በሚከተለው ድህረ ገጽ ማወቅ ይችላሉ፤ http://tinyurl.com/WhyGoogleDPS
በDPS ስለ ጉግል ጥያቄዎች ተጨማሪ መረጃና መልሶችን ለማግኘት የሚከተለውን ይዩ።

***<u>እኔ ይህንን አገልግሎት እንዴት እምቢ እላለሁ?</u>***

DPS ለተማሪዎ የሰጠውን ሂሳብ ለመጠቀም የሚይፈልጉ ከሆነ፣ በምዝገባ ሰነድ በወላጅ ፈቃድና መልቀቂያ ክፍል ላይ ምልክት በማድረግ (በተለምዶ *የወላጅ ፈቃድ ቅጾች* ተብለው የሚታወቁት) ተማሪዎን ከጥቅሙ ሊያስቀሩ ይችላሉ።



**ዘወትር የሚጠየቁ ጥያቄዎች እና**
**ለወላጆች/አሳዳጊዎች የተሰጡ መልሶች**

## አጠቃላይ የሂሳብ ጥያቄዎች

**ጥ1 የDPS የጉግል ሂሳብ ከጂሜይል ሂሳብ የሚለየው እንዴት ነው?**

*መ1፤ ለትምህርት ተቋም ጠቀሜታ ያላቸው የጉግል አገልግሎቶች ብቻ ናቸው በDPS የጉግል ግዛታችን የሚቀርቡት። አንዳንዳቹ በህዝብ ጉግል ሂሳብ ያሉ መሳሪያዎች በDPS የጉግል ግዛት አይገኙም። በተጨማሪ፣ ወደ የጉግል ግዛት የሚገባው በህዝብ ጉግል ሂሳብ (Gmail) ሳይሆን በተለየ የመግቢያ ገጽ ነው።*

**ጥ2፤ በDPS የጉግል ሂሳብ ኢሜይል ለልጄ ማድረግ እችላለሁ?**

*መ2፤ አዎን*

**መ3፤ ተማሪዬ በDPS የጉግል ሂሳብ ለሌላቸው የቤተሰብ አባላት ወይም ወዳጆች ኢሜይል መላክ ይችላል?**

*መ3፤ አዎን*

**ጥ4፤ ወላጆች የDPS የጉግል ሂሳብ መቀበል ይችላሉ?**

*መ4፤ በዚህን ጊዜ አይደለም። የራስዎን የጉግል ሂሳብ የሚከተለውን አድራሻ በመጎብኘት መክፈት ይችላሉ [https://accounts.google.com/SignUp](https://accounts.google.com/SignUp).*

**ጥ5፤ የልጄን የጉግል ሰነዶች ማየት እችላለሁ?**

*መ5፤ አዎን። ልጅዎ ሰነዶቹን ከርስዎ ጋር "Share" ወይም አጋራ በሚለው አማራጭ ሊያጋራዎት ይችላል፣ወይም በዚያው "Share" በሚለው አማራጭ ውስጥ ሰነዶቹን ማንኛውም ሰው እንዲያይ ማድረግ ይችላል።*

**ጥ6፤ ልጄ የጉግል ሂሳቡን በአግባቡ ባይጠቀም ሊከሰትበት የሚችለው ነገር አለ?**

*መ6፤ አዎን። የልጅዎ የጉግል ሂሳብ ጥቅም ነው፤ በአግባብ ካልተጠቀሙበት ይነጠቃል።*

**ጥ7፤ እኔ የጉግል የውይይት ክፍል (Google Chat) እቤት እጠቀማለሁ። ተማሪዬ ለምንድን ነው የማይጠቀመው?**

*መ7፤ በመላው ድስትርክት ውስጥ የመሳሪያውን ውጤታማነትንና አግባብነት ለመገምገም በአሁኑ ወቅት የጉግል የውይይት ክፍል ተዘግቶአል።*

## ከት/ቤት ውጭ ያሉ ጥያቄዎችን ማግኘት

**ጥ8፤ ልጄ የDPS የጉግል ሂሳቡን ከት/ቤት ውጭ መጠቀም ይችላል?**

*መ8፤ አዎን በWindows፣ Mac፣ወይም Chromebook ኮምፒዩቴር በሚሠራ መቅዘፊያና እንቴርኔት ሲኖር።*

**ጥ9፤ ተማሪዬ የDPS የጉግል ሂሳቡን ከእስማርት ስልኮች ለመግባት ይችላል?**

*ጥ9፤ አዎን፣ይሠራል፣ነገር ግን ድስትርክቱ በዚህ ጊዜ ሰነድ ወይም ድጋፍ በርሱ ላይ አይሰጥም።*

**ጥ10፤ እቤት እንቴርኔት የለኝም። ለተማሪዬ ምን ምንጮች ነው ያሉት?**

መ10፤ እንደ አጋጣሚ ሆኖ፣የDPS የጉግል ግዛት በእንቴርኔት ብቻ ነው የሚገባው። እንቴርኔት እቤት ከሌለ ልጅዎ በDPS የጉግል ሂሳብ ሊሠራ አይችልም። የህዝብ ቤተመጻህፍትና ምግብ ቤት የመሳሰሉት የህዝብ ሥፍራዎች ተማሪው ይህ አቅርቦት እንዲኖረው የሚያስችሉት ነጻ ሽቦ አልባ የሆነ የእንቴርኔት ግኙኝነቶችን ይሰጣሉ። በኮምካስት አማካይነት ደግሞ ዝቅተኛ ዋጋ ያለው የእንቴርኔት አገልግሎት አለ። ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣እባክዎን ttp://www.internetessentials.com ይጎብኙ።

**ጥ11፤ ተማሪዬ የDPS የጉግል ሂሳቡን ከሥራ ሰዓት በኋላ ለመግባት ይቸገራል፣እርሱ ማንን ሊገናኝ ይችላል?**

*መ11፤ እንደ አጋጣሚ ሆኖ፣ DPS ከሥራ ሰዓት በኋላ ለተማሪዎች ድጋፍ ሊሰጥ አይችልም። ችግሩን ለአስተማሪ ለመንገር ወደ ት/ቤት እስኪመለስ ድረስ መጠበቅ አለበት። አስተማሪው ደግሞ ለችግሩ መፍትሄ መሻት ለሚችለው ለት/ቤቱ የቴክኖሎጂ ተወካይ ጉዳዮቹን ያቀርባል።*

## በDPS የጉግል ሂሳብ ላለመቀበል የሚቀርቡ ጥያቄዎች

**ጥ12፤ እኔ ይህንን አገልግሎት ለተማሪዬ እንዴት እምቢ እላለሁ?**

*መ12፤ ተማሪዎ የተሰጣውን የDPS የጉግል ሂሳቡን እንዲጠቀም ካልፈለጉ፣በልጅዎ ምዝገባ ሰነድ ላይ የተማሪውን የኤሜይል ሂሳብ ለመተው ቅጽ ይሙሉ ወይም የት/ቤቱን ጸሀፊ ያነጋግሩ።*

**ጥ13፤ እኔ ልጄ በት/ቤት እንቴርኔት እንደይጠቀም መርጬአለሁ። ተማሪዬ አሁንም ወደ DPS የጉግል ሂሳቡ ውስጥ ለመግባት ይችላል?**

*መ13፤ እንደ ኢጋጣሚ ሆኖ፣ የDPS የጉግል ግዛት የሚገባው በእንቴርኔት ብቻ በመሆኑ፣ልጅዎ እኛ እንደ ድስትርክት የምናቀርባቸውን የDPS Gmail፣ Google docs፣ወይም ሌላ ማንኛውንም የጉግል መሳሪያዎች ለመጠቀም መሳተፍ አይችልም።*

**ጥ14፤ እኔ ልጄ የጉግል አፖችንእንደይጠቀም መርጬአለሁ። ተማሪዬ ሁሉንም የተሰጠውን ሥራ መሥራት ይችላል?**
*መ14፤ DPS ለሁሉም ተማሪዎች እኩል የትምህርት አቅርቦት ለማቅረብ ቆርጦ ተነስቶአል። ለትምህርት ጉግል አፖች ለተማሪዎችና ለአስተማሪዎች መሳሪያዎችን ለመገናኛ ፣ለትብብር፣ሲያቀርብ እና የተማሪን ተሳትፎ ሲያሻሽል፣ በአካል ስንኩልነት ምክንያት ልጆቻቸው ወይም ተማሪዎቻቸው ጉግል አፖችን እንደይጠቀሙ ወላጆቻቸው ለመረጡት፣ አስተማሪዎች ጉግል አፖችን ትምህርቶች በተለዋጭ እቅዶች እንዲያዘጋጁ ይደፋፈራሉ*

## የደህንነት ጥያቄዎች

**ጥ15፤ የተማሪዬ የDPS የጉግል ሂሳብ ተገቢ ያልሆኑ ቃላትን፣ስዕሎችን፣ ወዘ ተርፈ ለመለየት እንደሚጣራ ይገባኛል። ተማሪዬ ከት/ቤት ውጭ ኢሜይል ውስጥ ሲገባና ኢሜይል ሲልከና ሲቀበል የኢሜይል ማጣሪያው ይሠራል?**

*መ15፤ አዎን፣ የጋግል ኔት በሰው ቁጥጥር ማድረጊያ ዘዴ ነው። (http://tinyurl.com/GaggleHMS) ሁሉም ጽሁፍ፣ምስሎች፣፣እና ነገሮች ተገቢ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ከDPS የጉግል ግዛት የሚገባውንና የሚወጣውን ሁሉንም ኢሜይል ሂሳብ ያጣራል*

**ጥ16፤ የተማሪዬ የDPS ጂሜይል አስቀያሚ ነገር እንዳይደርስ ለማረጋገጥ ይጣራል፣ ይቆጣጠራልም ። ይህ በሌላ ጉግል አፕስ ይሆናል?**

*መ16፤ አይደለም፣በዚህ ጊዜ ከጂሜይል በስተቀር ለአፖች ማጣሪያ የለም። አስተማሪዎች ይዘቱን የመቆጣጠር ኃላፊነት አለባቸው እና እነዚህን መሳሪያዎች በመጠቀም ጥሩ ዜግነት እንዲማሩ በተማሪዎች እንመካለን።*

**ጥ17፤ ተማሪዬ ወደ DPS የጉግል ሂሳቡ ውስጥ ሲገባ ማስታወቂያ ያያል?**

*መ17፤ አይደለም፣ ተማሪው ወደ ጉግል ሂሳብ ከገባ ዘንድ በጉግል ግዛት ውስጥ ማስታወቂያ አያይም።*

**ጥ18፤ የእንቴርኔት ማስፈራሪያ እንዳይኖር ለመከላከል ምን እርምጃዎች ተወስደዋል?**

*መ18፤ DPS የተማሪ የእንቴርኔት ደህንነት እና በተለምዶ ስሜት ሚዲያ የእንቴርኔት ማስፈራሪያ የሚዳስሰውን የድጂታዊ ዜግነት መርኃ ግብር ይጠቀማል። Brian Dino (brian_dino@dpsk12.org) የDPS የተለምዶ ስሜት ሚዲያ ተወካይ ናቸው እና ለወላጆች፣ ለአስተማሪዎችና ለተማሪዎች መርኃ ግብሩ ምን እንደሚያካትትና ልጆቻችን እንዴት በደህና ሁኔታ እንደሚጠበቁ ለማወቅ ለማነጋገር አሉ።*

**ጥ19፤ ተማሪዬ የDPS የጉግል ሂሳቡን በመጠቀም የጉግል ሥፍራ መፍጠር ይችላል?**

*መ19፤ አይደለም፣ አስተማሪዎች ሥፍራ መፍጠር ይችላሉ እና ተማሪዎች ገጾችን ለመፍጠር እና/ወይም ኤዲት ለማድረግ ይፈቀድላቸው ወይም አይይፈቀድላቸው እንደሆነ ይቆጣጠራሉ። አስተማሪዎች ሥፍራው ለህዝብ ይታይ እንደሆነም ይቆጣጠራሉ።*

**ጥ20፤ ተማሪዬ በDPS የጂሜይል ሂሳብ በቤት ኮምፒዩቴር በሚያገኘው ኢሜይል የቤት የኮምፒዩቴርን የሚወር ቫይረስ ይመጣ ይሁን?**

*መ20፤ ቫይረሶችና ሌሎች መጥፎ ነገሮች የቤት ኮምፒዩቴርዎን የመውረር ስጋት ሁልጊዜ ሊኖር ይችላል። ነገር ግን፣ ይህ የሚፈልገው ልጅዎ በጎጂ ነገሮች መገናኛ ላይ ጫን ማድረግን ይጠይቃል። ተማሪዎች እንደዚህ ዓይነት ነገሮችን ከማድረግ ለመቆጠብ ደህና የኮምፒዩቴር ልምዶችን መማር አለባቸው።*

## ተጨማሪ ጥያቄዎች

**ጥ21፤ እኔ ሌሎች ጥያቄዎች አሉኝ፣ማንን ልገናኝ?**

*ጥ21፤ የተማሪዎ አስተማሪ ለአብዛኛዎቹ ጥያቄዎችዎ መልስ መስጠት መቻል አለበት እና እነርሱ መልስ ሊሰጡባቸው የማይችሉአቸው ጥያቄዎች ወደሚችለው አካል ዘንደ ይመራሉ።*

**ጥ22፤ ልጄ ቀድሞውኑ የራሱ ጂሜይል ሂሳብ ቢኖረውስ? ከDPS የጂሜይል ሂሳብ ይልቅ ይህንን ሂሳብ መጠቀም ይችላሉ?**
*መ22፤ አይደለም። ተማሪዎች የጉግል ድራይቭ ሰነዶቻቸውን ከDPS የጉግል ሂሳብ ጋር ሊጋሩ ይችላሉ ነገር ግን የDPS ለትምህርት አፖችንን ሙሉ በሙሉ ለመጠቀም የDPS የጂሜይል ሂሳቦችን መጠቀም አለባቸው።*